# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**<u>በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት</u>**

ቀን፡ **7/4 - 7/6/2019**
**አድራሻ፡** W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941 (Takes about 3 hours to 3:30 hours)
**Phone** = (920) 294-3323 Booking ID number= 14589
For making reservation please call during the below hours
**Sunday - Thursday 8:30-4:30**
**Friday - Saturday 24 hours**
**When reserving rooms please provide the date, the name Yemsrach how many people will be in the room.**

**<u>የአምልኮና የቃል ጊዜ ከወንድም ጌታያውቃልና ከእህት ብሩክታይት ጋር</u>**

በApril 14 ለያት ያለ የአምልኮና የቃል ጊዜ ከወንድም ጌታያውቃልና ከእህት ብሩክታይት ጋር ይኖረናል። ስለዚህ ፕሮግራም እየጸለያችሁ እንድትቆዩ ደግሞም በዚህ ፕሮግራም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድትሆኑ እናበረታታችኋለን። ጌታ ይባርካችሁ።

**<u>የአህቶች አገልግሎት ፕሮግራም</u>**

የሕቶች አገልግሎት ታላቅ የመነቃቂያና ቃሉን የመማሪያ ጊዜ አዘጋጅተዋል። ፕሮግራሙ የሚሆነው ቸርች ሲሆን ቀኑ በሚቀጥለው ቅዳሜ April 13, ከ3p.m. እስከ 5 p.m. ነው። እህቶች ሁሉ እንድትገኙ ተጋብዛችኋል። ለልጆችም ፕሮግራም ስላለ ልጆቻችሁን ይዛችሁ መምጣጣት ትችላላችሁ። የህቶች አገልግሎት አስተባባሪዎች። ጌታ ይባርካችሁ።



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"… ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት… ።"
(1ቆሮ. 11:25)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**April 7, 2019** | **መጋቢት 29፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | እትዬ ሰላም ምትኩ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| ቃል ............. | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።"

(1ቆሮ. 11:24-25)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ለመታሰቢያዬ አድርጉት

የእግዚአብሔር ቃል የጌታን እራት ስንወሰድ ለጌታ መታሰቢያ እንድናደርገው ያስተምረናል። ለመሆኑ የጌታን እራት ስንወስድ የምናስበው ምንድን ነው? አንደኛ በጌታ የተደረገልንን እናስባለን። ይህም ማለት ስለ እኛ ደህንነት የተቆረሰልንን የጌታን ስጋ እና የፈሰሰልንን የጌታን ደም እናስባለን። እንጀራውን ቆርሰን ስንወስድ የስጋው መቆረስ ምሳሌ ነው። ጽዋውንም ቀድተን ስንጠጣ የደሙ መፍሰስ ምሳሌ ነው። ይህ ደግሞ ለተካፈልነው ሕይወት መሰረት ነው። ጌታ ኢየሱስ በቃሉ እንዳለ የጌታን ስጋ የበላ ደሙንም ደግሞ የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። ከርሱ ጋራም ህይወትንና ትንሳኤን ይካፈላል (ዮሐ. 6:54,56)። እኛ ሕይወት ያገኘነው በጌታ ሞት ነው። ሞቱ የኛ ሞት ነው። በደሙም ከሃጢያታችን ታጠብን። በጌታ ሞት ከአብ ጋራ ታረቅን። በስጋው መቆረስ ለኛ ተዘግቶ የነበረው መጋረጃ ተቀዶ ወደ አብ የምንቀርብበት አዲስና ህያው መንገድ ተከፈተልን። ስለዚህም የጌታን እራት ስንወስድ አንዱ የምናስበው የጌታን ሞት ነው።

የጌታን እራት ስንወስድ የምናስበው ሁለተኛው ነገር ይህንን ስርዓት በእምነት ስናደርግ አሁን በሕይወታችን የሚሰራውን ነው። ቃሉ እንደምያስተምረን "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" ይለናል (1ቆሮ. 11:26)። እንጊዲህ ከእንጀራውና ከጽዋው ስንካፈል የጌታን ምት ለመናገር አቅም እናገኛለን። ይህም ማለት ሞቱን፣ በሞቱም ያገኘነውን ሕይወት እንዲሁም በሞቱ የተገለጸው ፍቅር በህይወታችን አዲስ ሆኖ መንፈሳዊ ግለትን ያመጣልናል። ስለዚህም ጌታ ወዶኝ ሞቶልኛል እንላለን፤ ለሌሎችም ይንን አስደናቂ እውነት እንመሰክራለን። እዚህ ላይ በክፍሉ እንደምናነበው የጌታን እራታ ሳይገባቸው (ሳይረዱት ወይንም ህይወታቸውን ሳይመረምሩ) የሚወስዱ ሁሉ ሊደከሙ፣ ሊታመሙ ሊያንቀላፉም ይችላሉ (ቁ. 30)። ይህ እንግዲህ የጌታ እራት በአማኙ ውስጥ የሚሰራው ስራ እንዳለ ያሳየናል። ሳይገባቸው የወሰዱ ከደከሙ፤ ተገብቷቸው የሚወስዱ ደግሞ ይበረታሉ። ሳይገባቸው የሚወስዱ ከታመሙ፤ ተገብቷቸው የሚወስዱ ደግሞ ይፈወሳሉ። ሳይገባቸው የሚወስዱ ካንቀላፉ፤ ተገብቷቸው የሚወስዱ ደግሞ የበዛ ሕይወት ይሆንላቸዋል።

የጌታ እራት በሶስተኛ ደረጃ የጌታን ዳግም ምጽአት ያሳስበናል። በቃሉ እንዳየነው እንጀራውን በበላን ጊዜና ጽዋውን በጠጣን ጊዜ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን እንናገራለን። በዚህ ቃል ውስጥ የጌታ መምጣት ተስፋ ተሰጥቶናል። ጌታችን ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት "ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" ብሎናል (ዮሐ. 14:1-3)። ጌታ ዳግመኛ ይመጣል። መጥቶም ወደ ራሱ ይወስደናል። ቃሉ የታመነና እውነት ነው። እንዲሁም ደግሞ ጌታ ይህንን ስርአት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲያደርግ እንዲህ አለ፡ "ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም" (ማቴ. 26:29)። እንግዲህ የጌታን እራት ስንወስድ ሌላው የምናስበው ከጌታ ጋር በእግዚአብሔር መንግስት እራት እንደምንካፈል ነው። ይህ የተባረከ ተስፋችን ነው። ጌታ ይመጣል። አዎን ማራናታ!